የሰበር መ/ቁ.18147

ቀን ሐምሌ 03/1998

ዳኞች:- 1- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3- አቶ ጌታቸው ምህረቴ

4- አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5- ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች:- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - አልቀረበም

መልስ ሰጭ:- አቶ ወንድወሰን አለማየሁ - ቀረበ

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር አንድ ሰራተኛ ከስራ የተሰናበተው በህገወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲመለስ በአዋጅ ቁጥር 42/85 መሰረት ሲወሰን ከስራ ታግዶ ለቆየበትና ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የስር ፍ/ቤት መ/ሰጭ ከስራ የተሰናበተው በህገወጥ መንገድ በመሆኑ ለታገደበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ስራው እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን ውሳኔውን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አጽንቶታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል፡፡

ለችሎቱም አንድ ሰራተኛ ከስራ የታገደውም በህገወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲመለስ በአዋጅ ቁ.42/85 መሰረት ሲወሰን ከስራ ስራ ለታገደለትና ስራ ላልሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 19-11-98

ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል።

ይህ ችሎት በመ/ቁ.17189 አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁ.42/85ን ድንጋጌዎች በመተርጎም ህጉ ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚፈቅድ አይደለም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል። በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ለመ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዝና ከሥራ ለታገደበት ጊዜ እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

## ው ሳ ኔ

- ይህ ችሎት መ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዙና ታግዶ ለቆየበት ጊዜ መከፈል ያለበት ሊከፈል አይገባም በማለት ወስኖ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.12715 ሰኔ 14 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.30975 ህዳር 28 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ፊ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን ፻9-11-98